# ትንቢተ ፡ ናሖም ።

(ክለሳ.1.20020507)

______________ትንቢተ ፡ ናሖም ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ ስለ ፡ ነነዌ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ፤ የኤልቆሻዊው ፡ የናሖም ፡ የራእዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቀናተኛና ፡ ተበቃይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ተበቃይና ፡ መዓትን ፡ የተሞላ ፡
ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ተቃዋሚዎቹን ፡ ይበቀላል ፥ ለጠላቶቹም ፡ ቍጣውን ፡ ይጠብቃል ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ትዕግሥተኛ ፥ ኀይሉም ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ በደለኛውንም ፦ ንጹሕ ፡ ነኽ ፡ አይልም ፤ እግዚአብሔር ፡
በወጀብና ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ መንገድ ፡ አለው ፥ ደመናም ፡ የእግሩ ፡ ትቢያ ፡ ነው ።

4 ፤ ባሕሩንም ፡ ይገሥጻታል ፥ ያደርቃትማል ፥ ወንዞችንም ፡ ዅሉ ፡ ያደርቃል ፤ ባሳንና ፡ ቀርሜሎስም ፡
ላልተዋል ፥ የሊባኖስም ፡ አበባ ፡ ጠውልጓል ።

5 ፤ ተራራዎችም ፡ ከርሱ ፡ የተነሣ ፡ ታወኩ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ቀለጡ ፤ ምድርና ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩበትም ፡ ዅሉ ፡ ከፊቱ ፡
ተናወጡ ።

6 ፤ በቍጣው ፡ ፊት ፡ የሚቆም ፡ ማን ፡ ነው ፧ የቍጣውንም ፡ ትኵሳት ፡ ማን ፡ ይታገሣል ፧ መዓቱ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡
ይፈሳል ፥ ከርሱም ፡ የተነሣ ፡ አለቶች ፡ ተሰነጠቁ ።

7 ፤ እግዚአብሔር ፡ መልካም ፡ ነው ፥ በመከራ ፡ ቀንም ፡ መሸሸጊያ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ የሚታመኑትንም ፡ ያውቃል ።

8 ፤ ስፍራዋን ፡ ግን ፡ በሚያጥለቀልቅ ፡ ጐርፍ ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፉታል ፥ ጠላቶቹንም ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ያሳድዳቸዋል ።

9 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የምታስቡት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋል ፥ መከራም ፡ ኹለተኛ ፡ አይነሣም ።

10 ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንደ ፡ ተመሰቃቀለ ፡ ሾኽ ፡ ቢኾኑ ፥ በመጠጣቸውም ፡ ቢሰክሩ ፡ እንደ ፡ ደረቅ ፡ ገለባ ፡
ፈጽመው ፡ ይጠፋሉ ።

11 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በክፉ ፡ የሚያስብ ፥ ክፋትን ፡ የሚመክር ፥ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቷል ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኀይለኛዎችና ፡ ብዙዎች ፡ ቢኾኑ ፡ እንዲሁ ፡ ይቈረጣሉ ፥ ርሱም ፡
ያልቃል ። እኔም ፡ አስጨንቄኻለኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላስጨንቅኽም ።

13 ፤ አኹንም ፡ ቀንበሩን ፡ ከአንተ ፡ እሰብራለኹ ፥ እስራትኽንም ፡ እበጥሳለኹ ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከስምኽ ፡ ማንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳይዘራ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ አዟል ፤ ከአምላኮችኽ ፡ ቤት ፡
የተቀረጸውንና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራውን ፡ ምስል ፡ አጠፋለኹ ፤ አንተም ፡ የተጠቃኽ ፡ ነኽና ፥ መቃብርኽን ፡ እምሳለኹ ።

15 ፤ እንሆ ፥ የምሥራችን ፡ የሚያመጣ ፡ ሰላምንም ፡ የሚያወራ ፡ ሰው ፡ እግር ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ነው! ይሁዳ ፡
ሆይ ፥ አጥፊው ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፍቷልና ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አያልፍምና ፡ ዓመት ፡ በዓሎችኽን ፡
አድርግ ፥ ስእለቶችኽን ፡ ክፈል ።

______________ትንቢተ ፡ ናሖም ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ የሚቀጠቅጥ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ወጥቷል ፤ ምሽግን ፡ ጠብቅ ፥ መንገድንም ፡ ሰልል ፤ ወገብኽን ፡ አጽና ፥ ኀይልኽንም ፡
እጅግ ፡ አበርታ ።

2 ፤ ዘራፊዎች ፡ ዘርፈዋቸዋልና ፥ የወይናቸውንም ፡ ዐረግ ፡ አጥፍተዋልና ፥ እግዚአብሔር ፡ የያዕቆብን ፡ ክብር ፡ እንደ ፡
እስራኤል ፡ ክብር ፡ ይመልሳል ።



www.ethiopianorthodox.org

3 ፤ የኀያላኑ ፡ ጋሻ ፡ ቀልቷል ፣ ጽኑዓንም ፡ ቀይ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ። ርሱም ፡ በሚያዘጋጅበት ፡ ቀን ፡ ሠረገላዎች ፡
እንደ ፡ እሳት ፡ ይንቦገቦጋሉ ፤ የጦሩም ፡ ሶማያ ፡ ይወዛወዛል ።

4 ፤ ሠረገላዎች ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ይነጕዳሉ ፣ አደባባይም ፡ ይጋጫሉ ፤ መልካቸው ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ነው ፣ እንደ ፡
መብረቅም ፡ ይከንፋሉ ።

5 ፤ መሳፍንቱን ፡ ያስባል ፤ በአረማመዳቸው ፡ ይሰናከላሉ ፤ ፈጥነው ፡ በቅጥሯ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፣ መጠጊያም ፡
ተዘጋጅለት ።

6 ፤ የወንዞቹም ፡ መዝጊያዎች ፡ ተከፈቱ ፣ የንጉሡ ፡ ቤትም ፡ ቀለጠች ።

7 ፤ ንግሥት ፡ ተገለጠች ፣ ተማረከችም ፣ ሴቶች ፡ ባሪያዎቿም ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ እየጮኹና ፡ ደረታቸውን ፡ እየመቱ ፡
ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይላሉ ።

8 ፤ ነነዌ ፡ ግን ፡ ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ ዠምራ ፡ እንደ ፡ ተከማቸ ፡ ውሃ ፡ ነበረች ፤ አኹን ፡ ግን ፡
ይሸሻሉ ፤ እነርሱም ፦ ቁሙ ፣ ቁሙ ፡ ይላሉ ፣ ነገር ፡ ግን ፣ የሚመለስ ፡ የለም ።

9 ፤ መዝገቧ ፡ መጨረሻ ፡ የለውምና ፣ የከበረውም ፡ የዕቃዋ ፡ ኹሉ ፡ ብዛት ፡ አይቈጠርምና ፡ ብሩን ፡
በዝብዙ ፣ ወርቁንም ፡ በዝብዙ ።

10 ፤ ባዶና ፡ ባድማ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ኾናለች ፤ ልብ ፡ ቀልጧል ፣ ጕልበቶችም ፡ ተብረክርከዋል ፤ በወገብም ፡ ኹሉ ፡
ሕማም ፡ አለ ፣ የሰዎችም ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ጠቍሯል ።

11 ፤ የአንበሳዎችም ፡ መደብ ፣ የአንበሳዎችም ፡ ደቦል ፡ የሚሰማራበት ፣ አንበሳውና ፡ አንበሳዪቱ ፡ ግልገሉም ፡ ሳይፈሩ ፡
የሚኼዱት ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

12 ፤ አንበሳው ፡ ለልጆቹ ፡ የሚበቃውን ፡ ነጠቀ ፣ ለእንስቶቹም ፡ ሰበረላቸው ፡ ዋሻውን ፡ በንጥቂያ ፣ መደቡንም ፡
በቅሚያ ፡ ሞልቶታል ።

13 ፤ እንሆ ፣ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፣ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ሠረገላዎቿንም ፡ አቃጥዬ ፡
አጤሳለኹ ፣ ሰይፍም ፡ የአንበሳ ፡ ደቦሎችሽን ፡ ይበላቸዋል ፤ ንጥቂያሽንም ፡ ከምድር ፡ አጠፋለኹ ፣ የመልክተኛዎችሽን ፡
ድምፅ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይሰማም ።

ትንቢተ ፡ ናሖም ፣ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ ለደም ፡ ከተማ ፡ ወዮላት! በኹለንተናዋ ፡ ሐሰትና ፡ ቅሚያ ፡ ሞልቶባታል ፤ ንጥቂያ ፡ ከርሷ ፡ አያልቅም ።

2 ፤ የዐለንጋ ፡ ድምፅ ፣ የመንኰራኵርም ፡ ድምፅ ፣ የፈረሶችም ፡ ኰቴ ፣ የፈጣን ፡ ሠረገላም ፡ ጩኸት ፡ ተሰምቷል ፤

3 ፤ ፈረሰኛው ፡ ይጋልባል ፣ ሰይፍም ፡ ይንቦገቦጋል ፣ ጦርም ፡ ይብለጨለጫል ፤ የተገደሉትም ፡ ይበዛሉ ፣ በድኖችም ፡
በክምር ፡ ይከመራሉ ፣ ሬሳቸውም ፡ አይቈጠርም ፤ በሬሳቸውም ፡ ይሰናከላሉ ።

4 ፤ ስለተዋበችው ፡ ጋለሞታ ፡ ግልሙትና ፡ ብዛት ፡ ይህ ፡ ኾኗል ፤ ርሷም ፡ በመተቷ ፡ እጅግ ፡ በለጠች ፣ አሕዛብንም ፡
በግልሙትናዋ ፣ ወገኖችንም ፡ በመተቷ ፡ ሸጠች ።

5 ፤ እንሆ ፣ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፣ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፣ ልብስሽን ፡ በፊትሽ ፡ እገልጣለኹ ፤ ኀፍረተ ፡
ሥጋሽንም ፡ ለአሕዛብ ፣ ነውርሽንም ፡ ለመንግሥታት ፡ አሳያለኹ ።

6 ፤ ርኵሰትንም ፡ በላይሽ ፡ እጥላለኹ ፣ እንቅሽማለኹ ፣ ማላገጫም ፡ አደርግሻለኹ ።

7 ፤ የሚያይሽም ፡ ኹሉ ፡ ከአንቺ ፡ ሸሽቶ ፦ ነነዌ ፡ ባድማ ፡ ኾናለች ፤ የሚያለቅስላትስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚያጽናናትንስ ፡
ከወዴት ፡ እፈልጋለኹ ፧ ይላል ።

8 ፤ አንቺ ፡ በመስኖች ፡ መካከል ፡ ከተቀመጠችው ፣ ውሃም ፡ በዙሪያዋ ፡ ከነበራት ፣ ምሽጓም ፡ ባሕር ፡
ከነበረ ፣ ቅጥሯም ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ከነበረ ፡ ከኖእ ፡ ዐሞን ፡ ትበልጫለሽን ፧



www.ethiopianorthodox.org

9 ፤ ኢትዮጵያና ፡ ግብጽ ፡ የማይቈጠር ፡ ኀይሏ ፡ ነበሩ ፤ ፉጥና ፡ ልብያ ፡ ረዳቶቿ ፡ ነበሩ ።

10 ፤ ርሷ ፡ ግን ፡ ተማርካ ፡ ፈለሰች ፤ ሕፃናቷ ፡ በመንገድ ፡ ዅሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተፈጠፈጡ ፤ በከበርቴዎቿም ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡
ተጣጣሉ ፥ ታላላቆቿም ፡ ዅሉ ፡ በሰንሰለት ፡ ታሰሩ ።

11 ፤ አንቺም ፡ ትሰክሪያለሽ ፡ ወራዳም ፡ ትኾኛለሽ ፤ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ከጠላት ፡ የተነሣ ፡ መጠጊያን ፡ ትፈልጊያለሽ ።

12 ፤ ዐምባሽ ፡ ዅሉ ፡ የመዠመሪያውን ፡ የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ እንደ ፡ በለስ ፡ ዛፎች ፡ ነው ፤ ቢወዛወዝ ፡
በሚበላው ፡ አፍ ፡ ውስጥ ፡ ይወድቃል ።

13 ፤ እንሆ ፥ በመካከልሽ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብሽ ፡ ሴቶች ፡ ናቸው ፤ የአገርሽ ፡ በሮች ፡ ለጠላቶችሽ ፡ ፈጽሞ ፡
ተከፍተዋል ፥ እሳትም ፡ መወርወሪያዎችኽን ፡ በልቷል ።

14 ፤ ከሰው ፡ ያስጨንቁሻልና ፥ ውሃን ፡ ቅጂ ፤ ዐምባሽን ፡ አጠንክሪ ፤ ወደ ፡ ጭቃ ፡ ገብተሽ ፡ ርገጪ ፤ የጡብን ፡
መሠሪያ ፡ ያዢ ።

15 ፤ በዚያ ፡ እሳት ፡ ይበላሻል ፥ ሰይፍ ፡ ያጠፋሻል ፥ እንደ ፡ ደጐብያ ፡ ይበላሻል ፤ እንደ ፡ ደጐብያ ፡ ብዢ ፥ እንደ ፡
አንበጣም ፡ ተባዢ ።

16 ፤ ነጋዴዎችሽን ፡ ከሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ይልቅ ፡ አበዛሽ ፤ ደጐብያ ፡ ተዘረጋ ፥ በረረም ።

17 ፤ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ ዘውድ ፡ የጫኑት ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፥ አለቃዎችሽም ፡ እንደሚንቀሳቀሱ ፡ ኵብኵባዎች ፡
ናቸው ፤ በብርድ ፡ ቀን ፡ በቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ ፥ ፀሓይም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ያኰበኵባሉ ፤ ስፍራቸው ፡ በየት ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ አይታወቅም ።

18 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እረኛዎችኽ ፡ አንቀላፍተዋል ፤ መኳንንቶችኽም ፡ ዐርፈዋል ፤ ሕዝብኽም ፡ በተራራዎች ፡
ላይ ፡ ተበትኗል ፥ የሚሰበስበውም ፡ የለም ።

19 ፤ ስብራትኽ ፡ አይፈወስም ፥ ቍስልኽም ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ወሬኽንም ፡ የሚሰሙ ፡ ዅሉ ፡ እጃቸውን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡
ያጨበጭባሉ ፤ ክፋትኽ ፡ ዅልጊዜ ፡ ያላለፈችበት ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነውና ፨



www.ethiopianorthodox.org